በንግድ ሽፋን የወንጀል ፍሬን ህጋዊ የማስመሰል ወንጀል

ንግድ የሰው ልጅ አንዱ የህይወቱ ዘርፍ በመሆን እንዴት እንደተጀመረ የተለያዩ ምክንያቶች ይጠቀሳሉ። ከእነዚህም ምክንያቶች መካከል የሰው ልጅ ቋሚ ቦታ ላይ መኖር መጀመሩ፤ የስራ ክፍፍል መፈጠሩ እና የምርት ውስንነት መኖር ናቸው። በሌላ በኩል በንግዱ ዓለም አንዳንድ አካላት  ህገወጥ ተግባራትን ሲፈፅሙ ይስተዋላል።

 በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ (money laundering) እና የተደራጁ ወንጀሎች (organized crimes) እርስ በርስ የሚመጋገቡ ወንጀሎች ናቸው። ከተለያዩ ወንጀሎች የመነጨ ሃብት ህጋዊ ለማስመሰል ወይም ለማጽዳት ወንጀለኞች የተለያዩ ስልቶችን ይጠቀማሉ። እነኚህ ህገወጥ ሰዎች በህገወጥ መልኩ ያገኙትን ገንዘብ  ህጋዊ አድርጎ ለመጠቀም ሶስት ዋና ዋና ስልቶችን ይከተላሉ።

አንደኛው ከወንጀል የመነጨን ገንዘብ ወደ ፋይናንስ ተቋማት ማስገባትና ማንቀሳቀስ ነው። ሁለተኛው ምንጩ ያልታወቀ ወይም ከወንጀል የመነጨውን ገንዘብ በጥሬ ማንቀሳቀስ ወይም ማዘዋወር ነው። ሶስተኛው መንገድ በዓለም አቀፍ ንግድ ሽፋን በወንጀል

የተገኘን ገንዘብ ማንቀሳቀስ፣ ህጋዊ ማስመሰልና መደበቅ ነው። በኢኮኖሚ ላይ የሚፈፀሙ የፋይናንስ ወንጀሎች በአገራት ሁለንተናዊ ዕድገትና ብልፅግና ላይ የሚያሳድሩት ጉዳት እጅግ ከፍተኛ ነው። እነዚህ ወንጀሎች የአንድ አገር ፖለቲካ እንዳይረጋጋ በማድረግ የዜጎች ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን የሚደፈጥጡ  እና  ማህበራዊ አገልግሎቶች እንዳይሻሻሉ የሚያደርጉ ጋሬጣዎች ናቸው። በመሆኑም የዓለም አገራት በኢኮኖሚ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን በዋናነትም በወንጀል ድርጊት የተገኘን ሃብት ህጋዊ አስመስሎ የማቅረብ ወንጀሎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ህጎች እና እነዚህን ህጎች ለማስፈፀም የሚያስችሉ ለተለያዩ ተቋማት የስራ ድርሻ ከፋፍለው ሰጥተዋል። ይህ ህገወጦችን የመቆጣጠር እርምጃ  ውጤታማ ስለመሆኑ አገራት በጋራ የሚገመገሙበት ዓለም አቀፍ ስርዓት ተበጅቷል። ይህን የሚያስተባብረው እና የሚመራው  ዓለም አቀፍዊ ተቋም  የፋይናንስ ድርጊት ግብረሃይል (Financial Action Task Force) ተብሎ የሚታወቅ ነው።

ከዚህ አለማቀፋዊ ተቋም ባሻገር ተመሳሳይ ሚና ያላቸው ቀጠናዊ ተቋማትም አሉ። ለምሳሌ ኢትዮጵያ አባል የሆነችበት የምስራቅና ደቡባዊ አፍሪካ አገራት የፀረ-በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ/ ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ ቡድን (Eastern and Southern African Anti-money Laundering Group-ESAAMLG) አንዱ ነው። በኢኮኖሚ ላይ ከሚፈፀሙ ወንጀሎች መካከል በዓለም አቀፍ ንግድ ሽፋን በወንጀል የተገኘን ሃብት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብና መጠቀም አንዱ መሆኑን ከላይ አይተናል።

ዓለም አቀፍ ንግድ ሲባል በዋናነት የተለያዩ ዕቃዎችንና ምርቶችን ከአንድ አገር ወደ ሌላ አገር መላክና መሸጥ ወይም ወደ አገር ውስጥ ማስገባትን ያካትታል። ይህም የወጪና ገቢ ንግድን ይመለከታል። በንግድ ሽፋን የሚፈፀም የወንጀል ፍሬን ወይም በህገወጥ መንገድ የተገኘን ሃብት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ ወንጀሎች ለተደራጁ ወንጀለኛ ቡድኖች፣ በተለያየ መስክ ፕሮፌሽናል የሆኑና የወንጀለኞች ህገ ወጥ የሃብት ምንጭ እንዳይታወቅ ለሚሰሩ አካላት እንዲሁም ሽብርተኝነትን በገንዘብ ለመርዳት ለሚፈልጉ አካላት ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር ነው። በሌላ በኩል ደግሞ የንግድ ስርዓት በተለይም ዓለም አቀፍ የንግድ ስርዓት በርካታ ውስብስብ ባህሪ ያሉትና የተለያዩ ሂደቶች ውስጥ የሚያልፍ በመሆኑ እና ወንጀለኞች በሙያተኞች ጭምር ታግዘው የወንጀል ድርጊታቸው በቀላሉ እንዳይደረስበት ከፍተኛ ጥረት የሚያደርጉ በመሆናቸው ወንጀሎቹን የመከላከልና መቆጣጠር ሃላፊነት ለተሰጣቸው ተቋማት ፈታኝ ያደርገዋል። በንግድ ሽፋን የተለያዩ የወንጀል ድርጊቶች ይፈፀማሉ። ከነዚህም መካከል ህገ-ወጥ የገንዘብ እንቅስቃሴ፣ የካፒታል ሽሽት፣ የጉምሩክ

እና ታክስ ጥሰት ተጠቃሽ ናቸው። በንግድ ሽፋን የሚፈፀም የወንጀል ፍሬን (በህገወጥ መንገድ የተገኘ ሃብት) ህጋዊ ማስመሰል ከዓላማው አኳያ በንግድ ላይ ከሚፈፀም ወንጀል የተለየ ነው።

በንግድ ሽፋን የሚፈፀም ወንጀል እና በንግድ ላይ የሚፈፀም ወንጀል ልዩነቱ ምንድን ነው? የሚለውን ማየት ተገቢ ነው። ንግድ በባህሪው ውስብስብ ሲሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ የተዘረጋ በርካታ የግብዓት ሰንሰለቶች ያሉት ነው። ይህን ነባራዊ ሁኔታ የተለያዩ የተደራጁ ወንጀለኛ ቡድኖች ያለአግባብ ለራሳቸው ጥቅም በማዋል በአገራት ላይ ጉዳት ያደርሳሉ። ከዚሁ ጋር በተያያዘ በተለያየ የህግና ንግድ ዘርፍ ሙያና ክህሎቱ ያላቸው

አካላትም የወንጀለኞች የወንጀል ድርጊት እንዳይደርስበት በማድረግ ከወንጀሉ ፍሬ በጋራ በዚህ ሂደትም ሙስናን ጨምሮ በተለያዩ መንገዶች የተገኘን ሃብትን ጨምሮ በውል የማይታወቁ በርካታ ገንዘቦችን በህገ-ወጥ መንገድ ማዘዋወርና ህጋዊ ለማስመሰል ይንቀሳቀሳሉ።

በዚህ ሂደት አገራት ተገቢውን ገቢ እንዳይሰበስቡና ለልማት እንዳያውሉ ማድረግ አንዱ ችግር ነው። ስለሆነም የወንጀል ፍሬን ማለትም ከወንጀል የተገኘን ሃብት ህጋዊ የማስመሰል ወንጀል ለመከላከልና ለመቆጣጠር ይህን ሂደት መግታት ይጠይቃል። ይህን ማድረግ የሚቻለው ደግሞ ወንጀለኞችን በወንጀል ተጠያቂ በማድረግ ወይም ሌላ ህጋዊ እርምጃ በመውሰድ ነው።

ለምሳሌ ወንጀለኛውን በእስርና ገንዘብ ከመቅጣት በተጨማሪ ከንግድ ስርዓቱ ውጪ ማድረግ ሌላው መንገድ ሊሆን ይችላል። በዓለም አቀፍ ንግድ ሽፋን የሚፈፀም የወንጀል ፍሬን ህጋዊ ማስመሰል ወንጀል ግብይትን ከትክክለኛ ዋጋቸው አሳንሶ (under invoice) ወይም አስበልጦ (over invoice) ማቅረብ ወንጀል ነው። በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ለማቅረብ ወንጀል ይህ አንዱ አመንጪ ወንጀል ተደርጎ ይወሰዳል።

የሚመለከታቸው የመንግስት ተቋማትና አካላት እነዚህን ወንጀሎች እና የአፈፃፀም ስልቶቻቸውን በጥልቀት በመረዳት አስተማሪ ህጋዊ እርምጃዎች እንዲወሰዱ የተቀናጀ ስራ መስራት ይጠይቃል። ከዚህ አንፃር የፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት ከተለያዩ የመረጃ እና ህግ አስከባሪ አካላት ጋር የመግባቢያ ስምምነቶችን በመፈራረም በመስራት ላይ ይገኛል።

ስለሆነም በወንጀል ነክ መረጃዎች ልውውጥ፣ በተሞክሮ ልውውጥ እና ሙያ ነክ ስልጠናዎችን በመስጠት ወንጀለኞች ከወንጀል ፍሬ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ እንዲሁም ይህ ወንጀል ለወንጀለኞች አክሳሪ እንጂ አትራፊ እንዳይሆን ትኩረት ተሰጥቶ በመሰራት ላይ ይገኛል። በንግድ ሽፋን የሚፈጸሙ የፋይናንስ ወንጀሎች አይነት በዚህ ጽሁፍ ለማሳያ ቀረበ እንጂ ወንጀለኞች የተለያዩ ስልቶችን የሚጠቀሙ ናቸው። ስለሆነም እንደ ባህሪው ክትትል ለማድረግ ከውጪ ሀገራት ጋር በትብብር እየተሰራ ነው።